ፓኖራማ ቁጥር 65

የትዝብት አድማስ

መጋቢት 20 2001 ዓም

" <u>የአይጥ ምስክር ድንቢጥ ፤ የባንዳ አወዳሽ ሹምባሽ</u> "

እንደ ፈረንጆቹ ቀን አቆጣጥር ባለፈው ሳምንት ማርች 12 2009 ዓም በአሜሪካ ምክር ቤት (ኮንግረስ) የውጭ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ ውስጥ የአፍሪካን ቀን አስመልክቶ አንድ ውይይት መካሄዱ ተገልጿል ። እዚህ ኮሚቴ ዘንድ በአስረጅነት ቀርቦ የዕማኝነት ቃሉን የሰጠው÷ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር የነበረው÷ አምባሳደር ዴቪድ ሽን የተሰኘ ሰው ነበር ። ሰውየው በአፍቃሪ ወያኔነቱ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚታወስ ነው ። ተጠቃሹ ሰው ቀደም ሲልም ወያኔን አዲስ አበባ በማስግባት የኢትዮጵያን የመከራ ምዕራፍ ለመክፈት የበቃውን የሎንዶንን ጉባዔ ለማዘጋጀት ከእነ ሄርማን ኮኽን ጋር በመተባበር ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተ እንደነበረም የሚዘነጋ አይደለም። በመሆኑም ሀገራችንን አስመልክቶ ሚዛናዊ ዕማኝነት ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቅ አልነበረም።ይልቁንም በተፃራሪው ያው እንደለመደው አሁንም አዲሱ የኦባማ አስተዳደር ለወያኔ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግለት ከመማፀን የሚቆጠብ አልሆነም።በአስረጅነት በመቅረብ ሊሰጠው የፈለገው ጉዳይ በጠቅላላው በአፍሪቃ ቀንድ ያሉ ሀገሮች ብሎ ስለፈረጀው ማለትም ÷ ኢትዮጵያ ÷ኤርትራ÷ ጅቡቲ÷ ሶማሊያና ሱዳን አስመልክቶ ቢሆንም ÷ ሰፋ ያለውን ጊዜ ያባከነው ግን በኢትዮጵያ ላይ ነበር ። በርግጥም በወያኔ ስር የወደቀችውን ሀገር ልክ እንደ ግል ወጀዱ አድርጎ ስለሚቆጥራት÷ የወያኔይቱን ኢትዮጵያ ለእኔ ተውሉኝ ካለ በርከት ያሉ ዓመታትን ያስቆጠረ ሰው ሆኗል ። በአሁኑ ወቅት ብሔራዊ መንግሥት የሌላት ኢትዮጵያ ሐገራችንም የማንም መጫዎቻ መሆኗ ከቶ የሚያስገርም ሊሆን አይችልም ።

ኢትዮጵያን አስመልክቶ ምስክርነቱን ለመስጠት ሲጀምር ÷ የአፉ መክፈቻና ያረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ያደረገው ÷ እንደ አውሮጳ ዘመን አቆጣጠር በ1991 ዓም አሜሪካኖች ወያኔን ሥልጣን ላይ ካወጡ ጀምሮ ÷ ዩናትድ ስቴትስ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ፖሊሲ በማስታወስ ነበር ።በዴቪድ ሺን አባባል ÷ አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የምትከተለው ፖሊሲ ያተኮረው ውስብስብ የሆኑትን ጉዳዮች ሚዛን ለመጠበቅ በሚያስችል አካሄድ ነው ።አሁንም ያ እንደሆነም አክሎ ተናግሯል። የወያኔ መሪዎች የአሜሪካንን

ጥቅም ማስጠበቅ ዓይነተኛ ዕምነታቸው በመሆኑ፥ በአካባቢው ያለውን የአሸባሪነት ስጋት ለማስተናገድ ተግተው ስለሚተባበሩ፥የቆየውን ሁለንተናዊ ተራድዖ አሜሪካ መቀጠል እንደ ሚኖርባት አሳስቧል። ምንም እንኳን አዲሱ የኦባማ አስተዳደር የታክቲክ ለውጥ ለማሳየት ቢከጅልም፥ አሸባሪነትን አስመልክቶ በሚያደርገው መመሪያ አሁንም የነመለሰ ዜናዊን አገልግሎት እንደሚያስፈለገው ሚስተር ሺን በአፅንዖት ተናግሯል ። ጊዜ የማይሸረውን የወያኔን አገልግሎትና ታማኝነት፥ ጠቀሜታና አስፈላጊነት የኦባማ አስተዳደር በቀላሉ ሊመለከተው አይገባም ሲልም ለነመለስ ዘናዊ ያለውን ውክልና አስረግጦ መስክሯል ። የአሜሪካንን የምሥራቅ አፍሪካ ፖሊሲን ለማስፈፀም ከመለስ ዜናዊ የበለጠ ታማኝ አገልጋይ ሊኖር እንደማይችል ያለውን ዕምነት ሲገልፅ ፥እንደ ማስረጃ ለማቅረብ የሞከረው እስከአሁን ድረስ፥ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ፥ የአሜሪካንን ሰላምና መረጋጋት አጠባበቅን አሰመልክቶ መለስ ዜናዊ የሚያደርገውን እንከን የማይወጣለት ታማኝ አገልግሎት በማውሳት ነው ። የመለስን በሶማሊያ ውስጥ በጦር ኃይል መግባት ፥ ያሜሪካንን ጥቅም እስካስጠበቀ ድረስ ፥ለሚ/ር ዴቪድ ሽን ጉዳዩ እንዳልሆነ ያለይሉኝታ ገልጿል። ይህ ግን ከቶ ሊያስገርም የሚችል አይደለም ፥ ለምን ቢባል ፥ ዴቪድ ሽን ለማስረዳት የጣረው ፥ የአሜሪካንን የውጭ ፖሊሲ በመሆኑ ነው ። ይኸ ደግሞ የማነኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲና ተግባር የተመሰረተው በዚያ ሀገር ዘላቂ ጥቅም ላይ መሆን አለበት የሚለውን መሠረታዊ ዓላማ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ነው ። ይህ መሠረታዊ ፖሊሲ ግን ፥ ወያኔዎቹን አይመለከትም ። ምክንያቱም የኢትዮጵያን ዘላቂና መሠረታዊ ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ያልተፈጠሩ በመሆናቸው ነው።

ከሁሉም ከሁሉም እጅግ የሚያስገርመው ግን ፥ዴቪድ ሺን ራሱን ያስገመተው የወቅቱን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዕድገት አስመልክቶ የሰጠው ምስክርነት ሆኖ አግኝተነዋል።፡
“ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ጥንካራ የኢኮኖሚ ርምጃ አስመዝግቧል ። ” ሲል በሀገሪቱ ሕዝብ ችግርና ሰቆቃ ላይ ምፀት ተናግሯል ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በረሀብ አለንጋ በሚገረፉባት ሀገር፥ በዋና ከተማዋ ብቻ 400 ሽ ወጣቶች በሥራ-አጥነት በሚቸገሩባት ኢትዮጵያ፥ ረሀብና ድህነት፥ በሽታና ስደት የኢትዮጵያ ብሔራዊ መለያ በሆነበት ምድር፥ መለስ ዜናዊ ኢኮኖሚውን አስመልክቶ ጠንካራ ውጤትን አስመዝግቧል ማለት ፥ ቢያንስ በሕዝባችን ድህነትና ረሀብ እንደ መሳለቅና ማላገጥ አድርግን እንቆጥረዋለን ። ሳሙኤል ጆንሰን የተባለ እንግሊዚያዊ ደራሲ ራሴላስ በተሰኘ መጽሐፉ “ ፍቅሬ ሥልጣኔን ባያሸንው ኖሮ ፥ የዐረብ ፈንጋዮች ደንገጡሬን አይወስዱብኝም ነበር ” ብላ ልዕልቷ ተናገረች ብሎ እንደጻፈው ሁሉ ፥ይህ አሜሪካዊ ፥ለነመለስ ዜናዊ ያለው ፍቅር፥ሚዛናዊነቱን ባይበክልበት ኖሮ ፥ እንዲህ ዓይነት ራስን የሚያዋርድ ምስክርነት ለመስጥት ባልበቃም ነበር ለማለት እንገደዳለን።

ከዚህም አልፎ ተርፎ ፥ መለስ ዜናዊ ለአማራጭ ሲል ምናልባት ወደ ሩሲያና ቻይና ጨርሶ ፊቱን እንዳያዞር ፥ ዩናይትድ ስቴትስ ብዙ ጫና ማድረግ እንደሌለባት አስጠንቅቋል ። በመሆኑም ፥ ስለ ሰብዓዊ መብት ረገጣ፥ ስለ ዲሞክራሲያዊ ሂደት፥ ስለ ፖለቲካ እስረኞች ሁኔታና እንዲሁም ስፍር ቁጥር ስሌለው የሀገሪቱ ስደተኞች መከራና ስቃይ ብዙ መግፋት፥ ለአሜሪካ ዲፕሎማሲ ብዙም እንደማይጠቅም ዴቪድ ሽን ለአሜሪካ ምክር ቤት ምስክርነቱን ለግሷል ። በአጭሩ ዩናይትድ ስቴትስ፥ የነመለስ ዜናዊን ታማኝ አገልጋይነትና ጥቅም አስጠባቂነት እንዲቀጥል ከፈለገች ፥ ወያኔን አሽሞንሙና መያዝ እንዳለባት አስረግጦ ተናግሯል።

እኛ እኮ ኢትዮጵያን አስመልክቶ በዩናይትድ ስቴትስ ኮንግሪስ ስለተሰጠው አስረጅነትና ምስክርነት ብዙ ተስፋና ጉጉት ይገኛል የሚል አመለካከት የለንም ። ኖሮንም አያውቅም ። ሊኖር ይችላል የሚል ቀቢፀ- ተሰፋ ለማስተናገድ የሚከጅሉ ክፍሎች ካሉም፥ እርማችሁን አውጥታቸው ሌላ መፍትሄ ለመፈለግ ተሰናዱ እንላለን ። በሌላ በኩል ደግሞ አዲሱ የኦባማ አስተዳደር ምናልባት ለኢትዮጵያ ልቡ ይራራላት ይሆናል ከሚል ተስፋ በመነሳት የፖለቲካ ተላላነትን ለሚያነፀባርቁ ዜጎቻችን፥ የኦባማ ቅድሚያና ትኩረት፥ የራሱን ውጥረት ማላላት እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ቅንጣት ያህል ደንታ አለመኖሩን እንዲገነዘቡት እናሳስባለን በውጭ ርዳታና ትብብር፥የሀገራችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ችግር በምንም ዓይነት መንገድና ሁኔታ ሊፈታ የማይችል መሆኑን ከምን ጊዜውም በበለጠ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንም ሳያሳስበው እርሱ ራሱ በሚገባ ያውቀዋል። ለዚህ ነው የዘረኞቹን ከፋፋይ ሥርዓት አምርሮ በመቃወም ላይ የሚገኘው ። ይህንን የሕዝቡን መራራ ተቃውሞና ትግል ለማኮላሸትንና አቅጣጫውንም ለማሳት፥ በአሁኑ ወቅት ሰፊ ግፊትና እጅ የመጠምዘዝ ሞከራ እየተደረገ ነው ። ይኸንን ግፊትና ተፅዕኖ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በማድረስ የወያኔን ዕድሜ ለመቀጠል የሚያስችሉ ሙከራዎች በሁሉም አቅጣጫ እየተደረጉ ናቸው ። ይህንን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግና በመጭው 2002 ዓም የወያኔ ምርጫ መጠነኛ የውሽልሽል ማስተካከያ ሂደት በማድረግ፥ ወያኔዎቹን እንደገና ለማስመረጥና የሕዝቡንም መከራና ስቃይ ለማራዘም መሰናዶው ተጀምሯል ። በአሁኑ ወቅት የሚደረጉት ሽር ጎዶች የሚከተሉትን ክስተቶችና ገቢሮች ለማሳካት የሚያስችሉ አቅጣጫ ጠቋሚዎች ናቸው።

1. ዛሬ፥ የውጭ ባዕዳን የመረጃ ሰዎች፥ ( እነ ስም -አይጠሬን ጨምሮ ) በአንድ በኩል፥ የሀገር ውስጥ የወያኔ ሰላዮች ደግሞ በሌላ በኩል በመተባበር፥ በከፍተኛ ደረጃ በመሯሯጥ ላይ እንደሚገኙ ተደርሶባቸዋል ። ይህንን ለማስፈፀም በሚሊዮን የሚቀጠር ገንዘብም በማፍሰስ ላይ ናቸው። ትግሉንም ለማኮላሸት ሌት - ተቀን በመማሰን ላይ ይገኛሉ።

2. እያረጀ-እያፈጀ በመውገርገር ላይ ያለውን ዘረኛ ሥርዓት ዕድሜ ለመቀጠል ታስቦ፥ መድረክ የሚባል የፈሪሳውያን ስብስብ ለማቋቋም ደፋ ቀና እየተባለ ነው። የዚህ መድረክ ግንባር ቀደም ተዋንያን፥የወያኔ ቀንደኞች የነበሩት አሁንም ዕትብታቸውን ለመቆረጥ ያሆነለቸው ስይ አብረሃና ገብሩ አሥራት የተሰኙ አውራ ወያኔዎች ናቸው። መድረካቸውንም ለማስፋት የብዙ ድርጅቶች በር በማንኳኳት ላይ ይገኛሉ ።በተለይም ተስፋ የቆረጡትን ክፍሎች የዓላማቸው ዒላማ አድርገው በማባበል ላይ ከመሆናቸውም በቀር፥ አማላጆችንም በየቦታው እየላኩ እንደሆነ ተደርሶባቸዋል።

3. ሰሞኑን በአሜሪካን ኮንግሬስ ውስጥ እነ ዴቪድ ሽን ያካሄዱት ድራማና ቲያትር በሚቀጥለው የወያኔ 2002 ዓም ምርጫ አገልጋያቸውን እንደገና ለማስመረጥ ከሚደረገው ዕቅድ ተለይቶ የሚታይ ሊሆን አይችልም። የሀገራችን የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ በውጭ ተጽዕኖና ግፊት እየተወሰነ ህልውናዋና ነፃነቷ እስከመቸ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ግን በርካታ ድርጅቶች ለምን እንደማይቆረቁራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትዝብት እንደሚከታተላቸው ሊያውቁት ይገባል።

4. “ ዝምብ ቢጠራቅም ግሬራ እንደማይከፍት ” ሁሉ፥ ከብዛት ጥራት እንደሚሻል ግን ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም ። ወያኔን ለማንበርከክ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆመው የሚያታገሉት አይበገሬ ልጆቹ ፥ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የውጭ ኃይል ተፅዕኖም ይሁን የሀገር ውስጥ አማላጅ ሊደፍራቸው አይችልም ። የሀገራቸውን ነፃነትና ልዕልና እንዲሁም የሕዝባቸውን አንድነትና እኩልነት ለማስገኘት የዓላማ ፅናታቸውና ከሕዝብ ጋር ያቆራኛቸው ሀገራዊ ቃል ኪዳን የትግላቸው ሰንደቅ መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ ።

በመሆኑም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ዛሬ- ፤

“ ከሀሰት መስካሪ፥ መጥፎ ተናግሮ ከመጥፎ አናጋሪ፥  
ሀገር ከሚሸጥ ባንዳ፥ ቃልኪዳን አፍርሶ ሕዝብ ከሚከዳ፥  
ታሪክን አዋርዶ፥ ዓላማን ከሚሸጥ ፥ ትግሉን ከሚጎዳ፥  
ከአይጥ ምስክር ከድንቢጥ፥ ከባንዳ አወዳሽ ከሹምባሽ፥  
ከፈረንጅ ነገረ-ፈጅ፥ ከአልኩባይ ቀላማጅ፥  
ሀገር ከፍሎ ሕዝብ አስፈጅ፥ ትግሉን ሊያስር እግር -ተወርች፥  
ከፀላዒ ሰናያት ከርኩስ -አጋንንት፥ ከክፍፍል ፅልመት“  
ያድነነ ከመኣቱ አያሳየን የወያኔን ዳግማዊ ምፅኣቱ ። ”

እያለ ሀዘኑን በፀሎቱ አጅቦ የሚታገለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠላቶቹን እንቅስቃሴ ነቅቶ እንዲጠብቅ፥ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን!!!!